**የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ወጣቶች ክንፍ ድርጅት(ኢሕአፓወክንድ)**
**Ethiopian People's Revolutionary Party Youth League (EPRP YL)**

# ሐገርና ሕዝብን የመታደግ ስብሰባ ጥሪ!

ዛሬ ኢትዮጵያ ሀገራችን የምትገኝበት ሁኔታ ከመቼውም ጊዜ በበለጠ እጅግ አሳዛኝ፤ አስጨናቂና አደገኛ መሆኑ በገሃድ የሚታይና የሚታወቅ ብቻ ሳይሆን ማንኛውንም ሀገር ወዳድና ለሕዝብ ቀናኢ የሆነን ዜጋ ሁሉ የሚያሳስበው እንደሆነ ግልፅ ነው።

ኢትዮጵያዊነት ለባዕድ ሳይቀር ትርጉም ያለውና አኩሪ ታሪካዊ ስያሜ ያለው ሆኖ ሳለ፡ ለወያኔ ግን ርግማን ሆኖ ቆይቷል። ኢትዮጵያ ብለው የተጋሉትንና መለያችን ኢትዮጵያዊነት ብቻ ነው፤ ቋንቋው መገናኚያችን እንጂ መለያያ አይደለም በማለት በጽናት የታገሉትንና እየታገሉ ያሉትን በጠላትንት ፈርጆ "አባይ፡ኢትዮጵያ" በሚል ተቀጽላ ከባዕዳኑም ተባብሮ ለማዳከምና ለማጥፋት የሚቻለውን ሁሉ አድርጓል።ዛሬም ይሁነኝ ብሎ በክልል ሽንሽኖ፤ አቃቅሮና አዳምቶ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን ለማዳካምና ለማጥፋት የረቀቀና የተቀናበረ ዘመቻውን ከምንጊዜው የበለጠ ተያይዞታል።

እነዚህን አስጊ ሁናቴዎች የተገነዘብን ኢትዮጵያዊን ሁሉ ለነገ የማንለው የታሪክ አደራ እንዳለብን ተገንዝበን የተባበረና የተጠናከረ ትግል ማድረግ እንደሚገባን ላፍታ መዘንጋት አይገባንም : :

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ከግማሽ በላይ የሆነው ወጣት ከምንጊዜውም በበለጠ የሀገሬ ጉዳይ ያገባኛል በማለት በሀገሩ ወሳኝ ሚና መጫወት እንዳለበት ስለምናምን ለሀገራችንና ለኢትዮጵያ ሕዝብ „ምን ማድረግ አለብን" በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ለመወያየትና ለመምከር ሕዝባዊ ስብሰባ ጠርተናል : :

**ኢትዮጵያ እንደ ኢትዮጵያዊነቷ ለመቀጠል ሕዝቧም በአንድነት**
**አብሮ ለመኖር ለሚፈልጉ ሁሉ**

በጀርመን ሀገር ለሚኖሩ፤ ኢትዮጵያ ከተጋረጠባት አደጋ ሊታደጓት የሚፈልጉ በዚህ የውይይት ስብሰባ ላይ ተገኝው በመፍትሄው ፍለጋ የበኩሎዎን አስተዋፅዖ እንዲያበረክቱ በጀርመን ኢሕአፓወክንድ ስም የከበረ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

**ቦታ፡ Adam-Klein Straße 6. Nürnberg 90429**
**ቀን: June 21 2014 (21/06/2014)**
**ሰዓት: 13:00-18፡00**

ወደ ስብሰባው ቦታ ለመምጣት በሕዝብ ትራንስፖርት ለምትጠቀሙ ከኑርንበርግ ዋና ባቡር ጣቢያ S1 ወደ Bamberg አቅጣጫ የሚጓዘውን በመያዝ እስከ Rothenburger Bahnhof ተጉዘው ይወርዱና 700 ሜትር በእግር ከተጓዙ የስብሰባውን ቦታ ያገኙታል። በመኪና ለሚመጡ የሚከተለዉን አድራሻ Adam Klein Straße 6 Nürnberg 90429 በመስጠት በቴክኖሎጂው ይጠቀሙ።

**ለበለጠ መረጃ፡** 015213231788, 015216711236